# ድርቅ የተቃውሞ አጀንዳ መሆኑ አብቅቷል!

ብ. ነጋሽ 02-24-17

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ከሕዳር 2009 መግቢያ ጀምሮ በመላ አገሪቱ በሚገኙ 246 ወረዳዎች 23 ቡድኖችን በማሰማራት ባከናወነው የዳሰሳ ጥናት 5.6 ሚሊዮን ሰዎች በድርቅ ሳቢያ ለምግብ እጥረት መጋለጣቸውን ይፋ አድርጓል። ኮሚሽኑ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ለማቅረብ 948 ሚሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልግም አስታውቋል። ባለፈው ዓመት ለምግብ እጥረት የተጋለጡት ዜጎች ቁጥር 10 ነጥብ 2 ሚሊዮን እንደነበረ ይታወሳል። እነዚህን ያለፈው ዓመት የምግብ እጥረት ተጋላጮች ለመርዳት መንግስት 16 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር መድቦ ነበር። በዚህም ድርቁ በሰው ህይወት ላይ ጉዳት ሳያደርስ መከላከል ተችሏል። የዘንድሮው ድርቅ በአመዛኙ የአርብቶ አደር መኖሪያ የሆኑ ቆላማ አካባቢዎችን ነው ያጠቃው፤ እነዚህም በኦሮሚያ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፣ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የደቡብ ኦሞ ዞን የሰገን ወረዳዎች፣ በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ዘጠኝ ያህል ዞኖች እንዲሁም የአፋር ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ናቸው።

ድርቅ የተፈጥሮ ክስተት ነው። በየትኛውም አገር በበለጸጉም ባልበለጸጉትም፤ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ፤- የአሜሪካዋ ካሊፎርኒያ ግዛት ላለፉት አምስት ዓመታት በከባድ ድርቅ ተመትታለች። አሜሪካ የበለጸገች አገር መሆኗ ድርቁን አላስቀረውም። ነገር ግን፤ ባለጸግነቷ የድርቁን ተጽእኖ ለመከላከል አስችሏታል። ዘንድሮ ኬንያና ሶማሊያም በድርቅ ተመትተዋል። የኬንያ መንግስት በቅርቡ ይፋ እንዳደረገው፣ በድርቅ ምክንያት 2 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎቹ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። በደቡብ ኬንያ ድንበር አካባቢ የሚገኙ አርብቶ አደሮች በድርቅ ሳቢያ ወደጎረቤት ታንዛንያ የተሰደዱ መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ። ደቡብ ሱዳንም እንዲሁ በድርቅ ተመትታለች።

ድርቅ አስከፊ ተጽእኖ የሚያሳድር ክስተት ቢሆንም፤ ከድርቅ ጋር ተያይዞ ትኩረት የሚያሰጠው ትልቁ ጉዳይ ድርቁ በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ለሰዎች ህይወት መጥፋትና ከመኖሪያ አካባቢ ለመሰደድ ምክንያት መሆኑ ነው። ይህ ሁኔታ ድርቅን ከሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች በተለየ ፖለቲካዊ ይዘት ያላብሰዋል። ጎርፍ፣ የመሬት

መነቀጥቀጥ፣ ማዕበል . . . የሚያደርሱት የሞትና የመፈናቀል ጉዳት ቅጽበታዊ በመሆኑ ፖለቲካዊ ገጽታ ተላብሶ መንግስትን ተጠያቂ አያደርግም። የድርቅ ተጽእኖ ግን ቅጽበታዊ አይደለም። ሲከሰት ይታወቃል። አሁን ባለንበት የስልጣኔ ዘመን ደግሞ አሰቀድሞ ይተነበያል። በኢኮኖሚ ላይ በሚያሳድረው ተጽእኖ ሳቢያ በሰዎች ላይ የሚደረሰው ጉዳትም ጊዜ የሰጣል። እናም ተዕእኖው በርትቶ ወደችጋርነት ተለውጦ ለሰዎች ህይወት መጥፋትና አካባቢን ለቅቆ ለመሰደድ ምክንያት ከመሆኑ በፊት ተጽእኖውን መከላከል ይቻላል።

ከተፈጥሮ አደጋዎች ሁሉ በተለየ ፋታ የሚሰጠውን የድርቅ ተጽእኖ መከላከል የመንግስትን ትኩረት፣ ችግሩ እንዲታወቀ ይፋ በማድረግ እርዳታ መጠየቅና ማቅረብ የሚያስችል ፖሊሲና ተቋማዊ ዝግጅት፣ በራስ አቅም እርዳታ ለማቅረብ አስቀድሞ ዝግጁ ሆኖ መጠበቅን ይጠይቃል። መንግስት መቼም ሊከሰት የሚችለውን የድርቅ አደጋ ችላ ብሎ አደጋው ደርሶ በሰዎች ላይ ጉዳት ቢያስከትል ተጠያቂ ከመሆን አያመልጥም። ድርቅ ከአደጋዎች ሁሉ በተለየ ፖለቲካዊ ገጽታ የሚኖረው በዚህ አኳኋን ነው።

በኢትዮጵያ በ1965-66 ዓ/ም እንዲሁም በ1976-77 የተከሰተው ድርቅ በዘውዳዊውና በወታደራዊው ደርግ ስርአት ላይ የፖለቲካ ተቃውሞ የቀሰቀሰው በዚህ ምክንያት ነው። በ1965-66 የተከሰተወና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ለችጋር የዳረገው፣ በመቶ ሺህ ለሚቆጠሩ ዜጎች ሞት ምክንያት የሆነው ድርቅ በወቅቱ ይፋ አልተደረገም። መንግስት ድርቁ ያስከተለውን ችጋር ሆን ብሎ ደብቆ ነበር። በዚህም ምክንያት የሊጋሽ አገራትንና የበጎ አድራጊ ድርጅቶችን እርዳታ በወቅቱ ማግኘት አልተቻለም። ዘውዳዊው መንግስት በራሱ አቅም እርዳታ ለማድረስም አልሞከረም።

ይህ በሆነ በ10ኛው ዓመት የተከሰተው የ1976-77 ረሃብም በተመሳሳይ ሁኔታ ነብስ አድን እርዳታ መቅረብ በነበረበት ወቅት ይፋ አልተደረገም ነበር። የወታደራዊው ደርግ መንግስት ድርቁ ወደችጋርነት ከመለወጡ አሰቀድሞ በጉዳዩ ላይ የተሟላ መረጃ የነበረው ቢሆንም፤ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ይፋ ማድረግ አልፈቀደም። ይህን ያደረገው እጅግ ዘግይቶ ሰዎች እንደቅጠል መርገፍ ከጀመሩ በኋላ ነበር። በምስጢርም እርዳታ ለማቅረብ አልሞከረም። ይህ ሁኔታ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በችጋር እንዲረግፉ ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ወታደራዊው ደርግ ለዚህ የዜጎች እልቂት ተጠያቂ ነው።

እንግዲህ፣ ድርቅ መቼም የትም ሊከሰት ይችላል። ድርቅ በመከሰቱ ብቻ ግን መንግስት ተጠያቂ አይሆንም። ይሁን እንጂ፣ መንግስት የድርቁን ተጽእኖ ለመቋቋም የሚያሳየው ተነሳሽነትና የሚያደረገው ጥረት አናሳ ከሆነ የፖለቲካ ተቃውሞና ተጠያቂነትን ያስከትላል።

ከወታደራዊው ደርግ መወገድ በኋላ ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በደርቅ ተመትታለች፣ ደርግ በተወገደ ማግስት በ1985-86፣ በ1994፣ በ2003፣ በ2007-8 እና ዘንድሮ በ2009 ዓ/ም። ይሁን እንጂ፣ ከእነዚህ መካከል የትኛውም ድርቅ ወደችጋርነት ተለውጦ ለዜጎች ህይወት መጥፋት፣ ከመኖሪያ ቄዬ መፈናቀል ምክንያት አልሆነም። በሽግግር መንግስቱ ወቅት በ1985-86 ድርቅ ሲከሰት አገሪቱ በራሷ እርዳታ የማቅረብ አቅም አልነበራትም። በተመሳሳይ 14 ሚሊዮን ያህል ዜጎች ለምግብ እጥረት ተጋልጠውበት እንደነበረ የተነገረለት የ1994 ድርቅ በተከሰተ ወቅትም አገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ ማቅረብ የሚያስችል አቅም አልነበራትም። በመሆኑም፣ መንግስት ድርቁ የከፋ ተጽእኖ ከማድረሱ በፊት ችግሩን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማሳወቅ፣ የእርዳታ ጠያቂ ግብረ ሃይል በማቋቋምና ወደለጋሽ ሃገራት በማሰማራት የዜጎቹን ህይወት ታድጓል።

ከ2003 ዓ/ም በኋላ የተከሰተው ድርቅ ተጽእኖ የተመከተበት መንገድ ግን ከበፊቶቹ የተለየ ነበር። የተለየ የሚያደርገው ደግሞ፣ አገሪቱ ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ሊውል የሚችል የመጠባበቂያ የእህል ክምችትየነበራት፣ እንዲሁም ለእርዳታ ዕህል ግዢ የሚውል በጀት የመመደብ አቅም መገንባቷ ነው። በ2003 ዓ/ም የአገሪቱ ምስራቃዊ ቆላማ አካባቢዎች በድርቅ ሲመቱ መንግስት ችግሩን ለለጋሾች አሳውቆ እርዳታ እስኪመጣ እጁን ሰብስቦ አለተቀመጠም። ከመጠባበቂያ የእህል ክምችት በማውጣት እርዳታ አቅርቦ ነበር። በ2007-8 በድርቅ ምክንያት ያጋጠመውን የምግብ እጥረት ለመከላከል የሚያስችል የ450 ሜትሪክ ቶን የመጠባበቂያ የእህል ክምችት ነበር። መንግስት ችግሩን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አሳውቆ እርዳታ እስኪደርስ ከመጠባበቂያ የእህል ክምችት ማቅረብ ጀምሮ ነበር። በኋላም 16 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በጀት በመመደብ ከውጭ አገር እህል በመግዛት እርዳታ አቅርቧል። የድርቁን ተጽእኖ በመከላከል ረገድ መንግስት የአንበሳውን ድርሻ ወስዷል።

የድርቁን ተጽእኖ በፍጥነት ይፋ በማውጣት የለጋሾች ድጋፍ እንዲገኝ የማድረግ፣ የእርዳታ አሰጣጥ ስርአት የመዘርጋትና ተቋም የማደራጀት፣ የመጠባበቂያ እህል ክምችት መያዝ፣

የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ በጀት በመመደብ ተጽእኖውን የመከላከል እርምጃ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት አገሪቱን መንግስት መለያ ባህሪይ ነው። በዚህም ከድርቅ ተጽእኖ ጋር ተያይዞ የሚነሳውን ፖለቲካዊ ሃላፊነት በሚገባ ተወጥቷል ማለት ይቻላል። በውጭ አገር የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ተቃዋሚዎች በአገሪቱ የተከሰቱትን የድርቅ አጋጣሚዎች ለተቃውሞ ፖለቲካ አጀንዳነት ለመጠቀም በተደጋጋሚ ሞክረው ያልተሳካላቸውም በዚህ ምክንያት ነው። አሁን አሁን የኢፌዴሪ መንግስትና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ የድርቅን ተጽእኖ በመከላከል ሃላፊነቱ ላይ እንደማይዘናጋ ስለተረዱ ድርቅን ለፖለቲካ ተቃውሞ አጀንዳነት ለመጠቀም ሙከራ ማድረግ ትተዋል።

ያም ሆነ ይህ፤ በጽሁፉ መግቢያ ላይ እነደተጠቀሰው አገሪቱ ዘንድሮም በድርቅ ተፅእኖ ስር ትገኛለች። የኢፌዴሪ መንግስትና ክልላዊ መንግስታት እንደተለመደው ድርቁ የአንድም ሰው ህይወት እንዳይቀጥፍ፤ ከመኖሪያ ቄዬ እንዳያፈናቅል፣ ለወጣቶችና ለህጻናት ትምህርት መቋረጥ ምክንያት እንዳይሆን አስፈላጊውን የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

የኢፌዴሪ መንግስት  የድርቁን ተጽእኖ ለመከላከል 1 ቢሊዮን ብር መድቦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በድርቁ ሳቢያ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ዜጎች ከአገሪቱ የመጠባበቂያ እህል ክምችት 141 ሺህ ሜትሪክ ቶን አውጥቶ እያቀረበ ነው። የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ እንዳስታወቀው፤ ከኤጀንሲው ሰባት መጋዘኖች በድርቅ ወደተጎዱ አካባቢዎች ዕህል እየተጓጓዘ ነው። በአሁኑ ጊዜም በአዳማ፤ በሻሸመኔ፤ በወላይታ ሶዶ፤ በሽንሌ፤ በኮምቦልቻ፤ በወረታና በመቀሌ ከሚገኙ የማከማቻ መጋዘኖች እህል እየወጣ ነው። በቀጣይም፤ በተደጋጋሚ ድርቅ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ፈላጊዎች ተደራሽ ለመሆን አዳዲስ መጋዘኖችን ለማቋቋም ጥናት መጠናቀቁን ኤጀንሲው አስታውቋል። ከሁለት ዓመታት በፊት የነበረው የኤጄንሲው 450 ሺህ ሜትሪክ ቶን የመጠባበቂያ ዕህል የማከማቸት አቅም ዘንድሮ ወደ 670 ሺህ ሜትሪክ ቶን አድጓል። በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን በፍኖተ ሰላም፤ በነቀምት፤ በነጌሌ ቦረና፤ በባሌ ሮቤ እና በሆሳዕና የእህል ማከማቻ መጋዘን በመገንባት የክምችት አቅሙን ወደ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ለማሳደግ አቅዶ እየሰራ መሆኑም ታውቋል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ ከፌዴራል መንግስት ጎን ለጎን በድርቁ የተጠቁ ክልሎች መንግስታትም እርዳታ በማቅረብ ተግባር ላይ ተሰማርተዋል። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች በ60 ሚሊዮን ብር ወጪ ድጋፍ እያደረገ ነው። የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልላዊ መንግስትም 300 ሚሊዮን ብር መድቦ ለድርቁ ተጽእኖ ምላሽ እየሰጠ ይገኛል።

የዘንድሮው ድርቅ ከአምናው በተለየ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ነው ያጠቃው፤ በመሆኑም፤ ለሰው ከሚሰጠው የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ እርዳታ በተጨማሪ ቢያንስ ለዘር የሚሆኑ እንስሳትን ለማትረፍ የከብት መኖ እርዳታም እየቀረበ ነው። እስካሁን በኦሮሚያ፤ በደቡብ እና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች በተከሰተው ድርቅ ምክንያት በእንስሳት ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመከላከል ከ200 ሺህ በላይ የሳር እስር መኖ መሰራጨቱን የብሄራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታውቋል።

በዚህ ረገድ የክልል መንግስታትም የራሳቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው። የደቡብ ክልል 100 ሺህ እስር ሳር፤ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል 70 ሺህ እስር ሳር በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች ማሰራጨታቸውን ተናግረዋል። ችግሩ ፋታ የማይሰጥ በመሆኑ በፓርኮች ውስጥ ያለ ሳር እየታጨደ ድርቁ በተከሰተባቸው ሶስት ክልሎች እየተከፋፈለ መሆኑም ታውቋል። የደቡብ ክልል፣ ውሃ ገብ በሆኑ አካባቢዎች በአስራ አምስት ቀናት የሚደርስ የከብት መኖ በማምረት ችግሩን በቀጣይ ለመከላከል እየሰራ ነው።

በአጠቃላይ፤ ድርቅ የአንድን አገር የልማት ደረጃ ሳይመርጥ፤ ወቅትና ቦታ ሳይለይ፤ መቼም የትም ሊከሰት የሚችል የተፈጥሮ አደጋ ነው። እንደማንኛውም የተፈጠሮ አደጋ ድርቅን ማስቀረት አይቻልም። ይሁን እንጂ፤ መንግስት ድርቅ በሰው ህይወትና በአጠቃላይ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደረሰውን ተጽእኖ መከላከልና መቀነስ የሚያስችል ስትራቴጂና ፖሊሲ፤ እንዲሁም የእርዳታ አሰጣጥ ስርአትና ተቋማዊ ብቃት ማዘጋጀት ይጠበቅበታል። አንድ መንግስት እነዚህን ሃላፊነቶች ካላሟላ ድርቅ የፖለቲካ ተቃውሞ አጀንዳ መሆኑ አይቀሬ ነው፤ ይህ መሆንም አለበት። በዚህ ረገድ የኢፌዴሪ መንግስት ከአገሪቱ አቅም አኳያ ሲታይ የድርቅን ተጽእኖ ለመከላከልና ለመቀነስ በቂ አቅምና ዝግጅት አለው። በእስከዛሬው የድርቅን ተጽእኖ የመከላከል ተግባርም ውጤታማ ሆኗል። እናም ድርቅ በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ አጀንዳ መሆኑ አክትሟል።